# አንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ (አ.ማ.)
# LION INSURANCE COMPANY (S.C)

## የባለአክሲዮኖች 16ኛ ዓመታዊ መደበኛ እና 7ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔዎች ጥሪ

በአዋጅ ቁጥር 1243/2013 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ንግድ ሕግ አንቀጽ 366፣ 393 እና 400 መሠረት የአንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ (አ.ማ.) የባለአክስዮኖች 16ኛ ዓመታዊ መደበኛ እና 7ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔዎች **ቅዳሜ ታህሳስ 20 ቀን 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 2:00 ሰዓት ጀምሮ** በአዲስ አበባ **ኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል** ይካሄዳል፡፡ በመሆኑም የኩባንያው ባለአክሲዮኖች በእለቱ እና በተጠቀሰው ቦታ በጉባኤው ላይ እንዲገኙልን የኩባንያው የዳይሬክተሮች ቦርድ በአክብሮት ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡

### ሀ/ የአስራ-ስድስተኛ ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳ፡-

1. የጉባኤውን ድምፅ ቆጣሪዎችን መሰየም፤
2. ምልዓተ-ጉባኤ መሟላቱን ማረጋገጥ፤
3. የጉባኤውን አጀንዳ ማፅደቅ፤
4. ከአስራ-አምስተኛ ጠቅላላ ጉባኤ በኋላ የተደረጉ የአክሲዮን ዝውውሮችን ማፅደቅና አዳዲስ ባለአክስዮኖችን መቀበል፤
5. እ.ኤ.አ. የ2022/23 የዳይሬክተሮች ቦርድ ዓመታዊ ሪፖርትን ማድመጥና ተወያይቶ ማፅደቅ፤
6. እ.ኤ.አ. የ2022/23 የሒሳብ ዘመን የውጪ ኦዲተሮች ሪፖርትን ማድመጥና ተወያይቶ ማፅደቅ፤
7. እ.ኤ.አ. የ2022/23 የሒሳብ ዘመን የተጣራ ትርፍ አደላደልና አከፋፈል ላይ ተወያይቶ መወሰን፤
8. የዳይሬክተሮች ቦርድ እ.ኤ.አ. የ2023/24 ወርሃዊ አበል እና እ.ኤ.አ. የ2022/23 ዓመታዊ የሥራ ዋጋ ክፍያን መወሰን፤
9. እ.ኤ.አ. ለ2023/24-2025/2026 የውጭ ኦዲተሮችን መሾምና የክፍያ መጠናቸውን መወሰን፤

### ለ/ የሰባተኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳ፡-

1. የጉባኤውን ድምፅ ቆጣሪዎችን መሰየም፤
2. ምልዓተ-ጉባኤ መሟላቱን ማረጋገጥ፤
3. የጉባኤውን አጀንዳ ማፅደቅ፤
4. የኩባንያውን የመመስረቻ ፅሁፍ ለማማሻል ተወያይቶ መወሰን፤
5. ተከፍለው ባላለቁት የኩባንያው አክሲዮኖች ላይ ተወያይቶ መወሰን፤
6. የኩባንያውን ካፒታል ለማሳደግ ተወያይቶ መወሰን፤

### ማሳሰቢያ፡-

- በስብሰባው ላይ መገኘት የማይችሉ ባለአክሲዮኖች በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ንግድ ሕግ አንቀፅ 377 መሠረት ጉባዔው ከመካሄዱ ከሦስት ቀን በፊት በአንበሳ ኢንሹራንሽ ሕንፃ ዋና መ/ቤት በመቅረብ ለዚሁ ዓላማ የተዘጋጀውን የውክልና ቅፅ ሞልተው በመፈረም ተወካይ መሾምና ተወካዩም የውክልና ማስረጃውን በማቅረብ የጉባኤው ተካፋይ ለመሆንና ድምጽ ለመስጠት የሚችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን፡፡
- የኩባንያው ባለአክሲዮኖች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በጉባዔው ላይ ለመሳተፍ ሲመጡ ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸውን የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፈቃድ ዋናውንና ኮፒ በመያዝ በጉባዔው ላይ መሳተፍ ይችላሉ፡፡እንዲሁም ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሆኑ የውጭ ሀገር ዜግነት ያላቸው የኩባንያው ባለአክሲዮኖች ትውልደ ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የቢጫ ካርድ ይዘው መቅረብ እንዳለባቸው በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡
- የኩባንያው የንግድ ምዝገባ ቁጥር፡ RK/AA/3/0002724/2006
  - የኩባንያው የተፈረመ ካፒታል፡ ብር 300 ሚሊዮን
  - የኩባንያው የተከፈለ ካፒታል: ብር 256.4 ሚሊዮን
- የኩባንያው ዋና መ/ቤት አድራሻ: አ.አ፣ ቦሌ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 04፣ የቤት ቁጥር 049 (አንበሳ ኢንሹራንስ ሕንፃ)

ፖስታ ሣ.ቁጥር፡ 26281/1000

ኢ-ሜል፡ lioninsurance@ethionet.et

ድህረ-ገጽ፡ http://www.anbessainsurance.com

በዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪ

**በአገልግሎቱ የሚረኩበት፣ በጥንካሬው የሚመኩበት!!**